
ፕሬስ የሕዝብ ዘብ ነው

# ጦቢያ

ጦቢያ 12ኛ ዓመት ቁጥር 7 የኅዳር 29 1997




## «ኢትዮጵያን መውጋት ድንች እንደመላጥ አይቀልም»

ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ

22373 ☎ 23-26-04
ሞባይል:- 09/207621
ፋክስ:- 251-1-23-26-05
akpac @telecom.net.et
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 3167
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣
አራት ኪሎ ቅርንጫፍ፣ አዲስ አበባ

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**
ግርማ ፈይሣ
09/40-31-10

**ዋና አዘጋጅ**
አረጋ ወልደቂርቆስ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አጥናፉ ዓለማየሁ

**ሪፖርተሮች**
ሁሴን ከድር
መሰንበት ኃይሉ

**ኮምፒዩተር ቅንብር**
አረጋሽ ፀጋዬ

**ኮምፒዩተር ጽሁፍ**
አዲስዓለም ደምሴ
ሲያባራ ወልዴ

**ሽያጭና ሥርጭት**
ሙሉጌታ ወ/ሚካኤል
ዳንኤል ወርቅነህ

**የፊት ገጽ ሽፋን ዲዛይን (አከፓክ)**

**አሳታሚ**
አጥቢያ ኮከብ የኅትመትና የማስታወቂያ ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር
አከፓክ

«ጦቢያ» መጽሔት ከሚያዝያ 1984 ጀምሮ በየወሩ የሚታተም፣
በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መጽሔት ነው::
መጽሔቱ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ያልወገነና
የግለሰቦችን ነጻ አስተያየት የሚያስተናብር ነው::

**አሥራ ሁለተኛ ዓመት፣ ቁጥር 7፣ የካቲት 29 1997**

## ኢትዮጵያዊ ጨዋነታችን የት ገባ?

«... የኢትዮጵያ ቀዳሚ ጉዳይ ሕዝቧ ነው:: ለሕዝቧ ጥቅም ለሕዝቧ ዋስትና የማይሰጥ በሕዝቧ ታምኖ ሕዝቧን የማያምን መንግሥት በሕዝቧ ያለው ተቀባይነት ምን ሊሆን እንደሚችል መናገር ይቸግረኛል:: እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል:: በሕዝብ መካከል እንደልብ መንቀሳቀስ ለቆሙለት ሕዝብ ክብሩና ማዕረጉ ነው:: የማኅተመ ጋንዲን ታሪክ የምናስታውሰው በከበሬታ ነው::»

*ዳንዔው ሠርቤሎ* .....ገጽ 4

## ሳይቃጠል በቅጠል

«አሁን እኔ ቀልባችሁን ለመሳብ የፈለኩት የጠረፍ አካባቢዎቻችን ወደ ሆኑት የጋምቤላና የሱማሌ ክልሎች ነው:: እነዚህ ክልሎች አሁን በተያዘው ሁኔታ ከቀጠሉ ወደፊት ከኢትዮጵያ ግዛት መገንጠላቸው አይቀሬ ነው:: ይኸ ደግሞ ሟርት ሳይሆን አንዳንድ ከታዘብኳቸው ሁኔታዎች ተነስቼ የተነበይሁት ነው::»

*መርዕድ ከበደ* ....ገጽ 10

## «ግብፅ ኢትዮጵያን ለውሃ ብላ መውጋት ድንች የመላጥን ያህል አይቀላትም»

«... በእኛ ውሃ ሌሎች ስርተውበት ሲበለጽጉ እኛ ዓይን ዓይኑን እያየን እንዴት በድህነት አረንቋ፣ በልመና ሃፍረት ውስጡ እንኑር?! ውሃን ለልማት ብናውል ምን ይቸግራል? ጫና ባለበት መንገድ አይደለም:: አመቺና ቀላል በሆነ መንገድ በተከታታይ ማድረግ ይቻላል::»

*ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ* .....ገጽ 7

## ምሥርና ኢትዮጵያ ከፈርኦኖች እስከ ዛሬ

«ጥንት በፈርኦኖች ዘመን የተቀየሰው ኑቢያን የመውረርና አባይን የመቆጣጠር ዓላማ በዘመናዊት ግብፅም ችላ አልተባለም:: እንዲያውም ዓላማውንና ስልቱን እያሰፋ እስከ ባድመ ጦርነት ዘልቋል...»

*ማሞ ውድነህ* .....ገጽ 13

## በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት የኢሰመጉ ምሥክርነት

«ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ፣ በሕይወት ላይ፣ በአካል ላይ ተደጋጋሚ ጥሰቶች ተፈጽመዋል፣ ሰዎች ያለ ሕግ ተገድለዋል፣ ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ያሉበት እንዳይታወቅ ተደርገዋል በማለት መግለጫዎች ወጥተዋል:: ይህን የፈጸሙ የመንግሥት አካል አባላት ወደሕግ እንዲቀርቡ በማለት የቀረቡ ጥያቄዎች ታፍነዋል::»

*አቶ አበበ ወርቄ* .....ገጽ 22

## ጓዳችን

«የ2020 ኢትዮጵያ ካለ ዴሞክራሲና ልማት ሰላምን፣ ካለ ሰላምና ልማት ዴሞክራሲን፣ ካለ ሰላምና ዴሞክራሲ ልማትን ማምጣት በእጅጉ ይቸግራታል ብዬ ስለማምን ፈተናው ቢበዛም ሦስቱንም በጥምረት የምናገኝበትን መንገድ መፈለግ አለብን ብዬ አምናለሁ::»

*ዶክተር ታደሰ ኪርስሞ* .....ገጽ 16

## ሌሎች

◆ ከመልዕክት ሣጥናችን 2፣ ◆ ከአዘጋጁ ቢሮ 3 ◆ ጓዳችን16 ◆ የቋንቋ ቃና 19
◆ የመነጋገሪያ መድረክ 13 ◆ ሕይወታችንን እንታደጋት 20 ◆ ሙሽዘር 25
◆ ማኅበራዊ ኪን 29 ◆ ልዩ ጥንቅር 22 ◆ ማኅበረሰብ 27 ◆ ቅኝት 37



# ማኅበራዊ



# ኪን




ይህ ዓምድ ማኅበራዊ ጉዳዮችን፣ ኪነ-ጥበባዊ ዕሴቶችንና ባሕላዊ ትውፊቶችን የያዙ ጽሑፎች ይስተናገዱበታል።

አዘጋጅ ሁሴን ከድር

# ዶ/ር ነገደ በመጽሐፋቸው ምን አሉ?



ዶ/ር ነገደ ጐበዜ




*የመጽሐፍ «ገላጭ» ግምገማዊ አስተያየት*
*ርዕስ - ሕገ-መንግሥት፣ ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ (ከትላንት ወዲያ እስከ ነገ)*
*ደራሲ - ዶ/ር ነገደ ጐበዜ*
*የገጽ ብዛት - 208 (እ.ኤ.አ በ2004 በአሜሪካ በአሶፕ አሳታሚዎች ዋሽንግተን ዲሲ ታተመ)*
*አስተያየት - በግርማ ፈይሣ*

*ከሁሉ በፊት የዚህን መጽሐፍ ግምገማ ስናደርግ ከመጽሐፉ ይዘት አንጻር አጠቃላይ ዳሰሳ ለማድረግ ነበር። እንዳጋጣሚ እሁድ የካቲት 21 ቀን 1997 በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዙሪያ ተካሂዶ በነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት በአቶ በረከት መጽሐፉ ሲጠቀስ ስናይ የአቶ በረከት ከመጽሐፉ ጠቅሰው ያቀረቡትን ብቻ ነው ወይስ ሌላም ቁም ነገር አለው የሚለው ይበልጥ አወያየን። አንባቢያን የመጽሐፉን መልዕክት ይረዱት ዘንድ አስተያየታችንን እንዲህ አስፍረናል።*

ወደፊት ለመዝለል ወደኋላ መንደርደር ያስፈልጋል። ለግንቦቱ ምርጫ የኋሊት መንደርደርና መሟሟቅ ተጀምሯል። በተወዳዳሪ የፖለቲካ ማኅበሮች መካከል ክርክሩ እየጦፈ ነው። እንደ ኦሎምፒክ ስፖርት ለአራት ዓመቱ የፖለቲካ ትግል የማጣሪያ ውድድር ከተጀመረ ውሎ አደረ። በራስ ተነሳሽነት ይመስለኛል አንዳንድ ጋዜጦች ነጥብ መስጠትም ጀማምረዋል። ሁኔታውን በጉጉት እየተከታተልኩ ማንን ልምረጥ እያልኩ ማውጠንጠን ከጀመርኩ ሰነበትኩ። ሳላስበው ከፖለቲካው ምርጫ ጋር ተዛምዶ ያለው ሰሞኑን ታትሞ የወጣ የፖለቲካ መጽሐፍ እጄ ገባና መላልሼ አነበብኩት።

መጽሐፉን ብዙ ሰዎች አግኝተው ቢያነቡት ኖሮ ስለ አገራችን ሕገ-መንግሥት፣ ስለምርጫና ስለዴሞክራሲ ባህል ታሪክና ስለወደፊቱ አቅጣጫ ጠቃሚ መረጃ ሊያገኙበት በቻሉ ነበር የሚል ቁጭት አደረብኝ። ይሁንና መጽሐፉ በቀላሉ የሚገኝ አልመሰለኝም። ስለዚህ ለምን ሓሳቡን ጠቅለል አድርጌ ቢያንስ ለመጽሔታችን አንባቢዎች አላቀርበውም ብዬ አሰብኩ። ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ተመካከርኩና «ገላጭ አስተያየት» እንድጽፍ ተስማማን። አስተያየቴን ልጽፍ የፈለግሁበት ዓላማ ይኸው ነው።

«ገላጭ አስተያየት» የሚለውን ሐረግ የቀነፍኩት ይሁነኝ ብዬ ነው። እንደወጉ በመጽሐፍ ላይ የሚቀርብ አስተያየት (Book reviewien) ሁለት ፈርጅ አለው። አንዱ ገላጭ ሁለተኛው ሒሳዊ ነው። ይኸኛው ይዘቱን መተመንን (evaluation) አምጡ ይላል። እያነፃፀሩ አንዴ በዘመን የኋሊት መሄድና ማጣቀስን፣ አንዴ ደግሞ በወቅቱ ካለው ሁኔታ ጋር እያነፃፀሩ የወደፊቱንም አቅጣጫ እያመላከቱ ሥራውን ለአንባቢ ፍርድና ብይን ማቅረብን ይጠይቃል። እኔ የፖለቲካ ማይም ነኝና በዚህ በሒሳዊ አስተያየቱ መስመር አልገዝም።

ሌላው «ገላጭ» አስተያየት የተባለው ነው። ይኼኛውም ቢሆን ቀላል አይደለም። የራሱ የሆኑ አካሄዶች አሉት። እዚህ ላይ መዘርዘሩ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። የሆነ ሆኖ መጽሐፉን በሙሉ ከዳር እስከዳር በጥንቃቄ አንብቦ ማጠቃለያ ሳይሆን ደራሲው ምን ለማለት እንደፈለገ ወይም የመልዕክቱ ዓላማ ምን እንደሆነ አንባቢ በቀላሉ ሊረዳ በሚችለው መልክ ማሳየትን ይጠይቃል። ይዘቱ ወቅታዊ መሆኑንና ለአንባቢያን ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን መጥቀስ ያሻል። ከበፊቱ ጋር ያለው ልዩነት ይኸኛው በቀጥታ ይዘቱን የማይገመግም መሆኑ ነው። እንዲህ ሲባል ግን አስተያየት አቅራቢው አስተያየት ሊጽፍ የተነሳበትን ምክንያት መሠረት በማድረግ በተዘዋዋሪም መንገድ ቢሆን አንዳችም ምዘና አያደርግም ማለት አይደለም። የድርሰቱን ዓላማ ተረድቶት ከሆነ መረዳቱን የሚያስረዳበት አንዱ መንገድ ሚዛንን ሊጠይቅ ይችላል።

ከታሪክ አንጻር ሲታይ በወንዶች ሰብዓዊ መብት መከበር ላይ ተመሥርቶ የመጀመሪያ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የተካሄደው እ.ኤ.አ በ1848 ዓ.ም በፈረንሣይ አገር ነበር። አብዮቱ ከተካሄደ ከ6 አሠርት ዓመታት በኋላ ማለት ነው ዛሬ ላይ ቆመን ስለ ዴሞክራሲያዊና ስለ ሥር ነቀል ምርጫ ስናነሳ ቀላል ይመስለን ይሆናል። በወቅቱ ግን እጅግ ከባድ ነገር ነበር። የአቶ አክሊሉ ኃ/ወልድ ካቢኔ ፈርሶ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠ/ሚኒስትር ሆነው በተመደቡ ጊዜ ለሕግ-መምሪያ ምክር ቤት ቀርበው ከነበሩት ረቂቅ ሕጐች መካከል አንዱና መዘዘኛው የባለርስቶችንና የጢሰኞችን ግንኙነት ለመወሰን የቀረበው ረቂቅ ነበር። የምክር ቤቱ አባላት በሙሉ ባለርስቶች ነበሩ ማለት ይቻላል። «ጢሰኛውን ከሲሶ ምርቱ በላይ ግብር ማስከፈል አይቻልም፣ ከመሬቱ ላይ

መንቀልና ማባረር አይቻልም ወዘተ...» የሚል የሕግ ረቂቅ እንዴት ተደርጐ ነበር በራሳቸው በባለርስቶቹ ማጽደቅ የሚቻለው? በጣም ከባድ ነገር ነበር::

የፈረንሣይን ሥርወ መንግሥት ተከትለው የነገሡትን ንጉሥ ፊልፕን እንዴት አድርጐ ነው በምርጫ ከዙፋን ማውረድ የሚቻለው? ግን ተቻለ:: እጅግ ሰልጥነዋል በተባሉት በእነ እንግሊዝና አሜሪካ ያልታየ ከ9 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለምርጫ ወጣ:: ያን ጊዜ ከፈረንሣይ ሕዝብ ከ30 ሚሊዮን ውስጥ ለመምረጥ የሚያስችለውን ቀጭን መስፈርት የሚያሟላው 170 ሺ ሰው ብቻ ነበር:: 9 ሚሊዮን ሕዝብ ግልብጥ ብሎ የወጣው አምፆ ነበር:: እምቢኝ፣ አሻፈረኝ የሚል አቋም ይዘው የተነሱት ንዑስ ከበርቴዎችና ወዝ አደሮች (ላባደሮች) ንጉሡን ከሥልጣን አውርደው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አቋቋሙ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ተአምር ተሠራ::

የሞት ቅጣት ፍርድን አስቀረ፣ በፈረንሣይ ግዛተ-ክልል የባርያ ፍንገላንና የሰው ንግድን ሥርዓት በአዋጅ አስቀረ፣ የአንድ ቀን የሥራ ሰዓት ወደ 10 ዝቅ እንዲል ወሰነ፣ የፕሬስ ነፃነትን አወጀ፣ የመሥራትን መብት፣ ሥራ ካልተገኘ የማኅበራዊ ዋስትና አስከብሯል:: ሌሎችም ሥር-ነቀል እርምጃዎች በፈረንሣይ ሊወሰዱ የቻሉት ሕገ-መንግሥታዊ ለውጥ በመደረጉ ነው::

ይህ ነጥብ ወደ ተነሳሁብት ወደ ዶ/ር ነገደ ጐበዜ መጽሐፍ ግምገማ ይወስደኛል:: ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት መነሻ ምክንያት ሆኗቸዋል ብዬ የምገምተው በአገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ይልቁንም በመጪው ግንቦት ለሚካሄደው 3ኛው የፖለቲካ ምርጫ ተቃዋሚ ክፍሎች ተባብረው ገዢውን ፓርቲ ለማሸነፍ ከመታገል ይልቅ «መከረኛው ሕዝባችን <ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ> እያለ የሚደጋግመውን ሮሮ ላለመስማት አውቀን የተኛን ይመስል ትግሉ «በመሟሟቅ» ላይ ያለው «በኛና በነሱ» መካከል ሳይሆን ጭራሹኑ በተቃዋሚዎች መካከል እየሆነ መምጣቱን» በመታዘብ ሁኔታው ከቀጠለ «የሀገራችንና የሕዝባችን ዕጣ ፈንታ <የሚሸሹብት ምሽግ ሲሸሽ ታየ>የሚባለው ዓይነት እንዳይሆን ሥጋት እንዳላቸው ገልጸው መደረግ ያለበትን ለመጠቆም ሲሉ የፃፉት መጽሐፍ አድርጌ ነው የወሰድኩት::

ከመጽሐፉ ይዘት የተገነዘብኩት ሌላው ዓቢይ ምክንያት ዋናው የትግል ዓላማ መሆን ያለበት 5 ዓመት እየጠበቀ የሚመጣው የምርጫ ግርግር ወይም በምርጫው መሳተፍና አለመሳተፍ ዙሪያ በሚደረግ ክርክር ዙሪያ ሳይሆን አስቀድሞ ነገር በኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ሥር እስካለን ድረስ የምርጫ ሂደት ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ማምጣት ምን ሚና ሊኖረው ይገባል የሚለው ቁም ነገር ነው:: ስለዚህ ጉዳይ ዶ/ር ነገደ ጐበዜ በመጽሐፋቸው መቅድም ላይ ያሰፈሩት ሓሳብ ሊጠቀስ ይችላል፤

*«በኛ ግምት የዚህ ሕገ-መንግሥት ሥርዓት መቀየር ጉዳይ ሀገራዊ የጋራ አጀንዳ ነው:: እንዳልባሌ ጉዳይ ከቆጠርነው ኅብረተሰቡንም ሆነ ዓለማቀፍ ክምንዩቲውን የምናንቀሳቅስበት የጋራ ስትራተጂ አይኖረንም:: በዚህ የትም አይደረስ:: ይህ አጀንዳ ተረስቶ ክርክሩ በተሳትፎና በቦይኮት ጥያቄ ላይ ብቻ ከሆነ ድኀረ ግንቦቱ ሁኔታ ምን ይሆናል «ተሳታፊዎቹ» የተቆረጠላቸውን መቀመጫ አግኝተውና በተቃዋሚነት ፓርላማው ውስጥ ተሰይመው፣ በሕዝብ ተረስተው «ትግሉን» ይቀጥላሉ:: የቦይኮት ደጋፊዎችም እስከሚቀጥለው «መሥፈርቶች በተሻለ የሚሟሉበት» ምርጫ ድረስ የሚባል ጠፍቶ ትግሉን «ብሌላ ዘዴ» ማለትም በአትርሱን መልክ በሚወጡ የተቃውሞ መግለጫዎች ይያያዙታል::*

ደራሲው በመጽሐፋቸው ሊያስተላልፉ የፈለጉት መልዕክት ወይም የድርሰቱ ዓላማ (Purpose) ከላይ በጥቅስ ውስጥ የሰፈረው ይመስለኛል:: አቀራረቡን በተመለከተ ምናልባት በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጡት ሐረጐች የአገራችንን የወቅቱን ሁኔታ ለሚከታተል ሰው ፖለቲካዊ አሸሙሩ ሊገባው ስለሚችል ችግር ላይኖረው ይችላል:: የወቅቱ ፖለቲከኛ ግን ከታሪክ አኳያ ሲታይ አልፎ ሂያጅ ነው:: «ተሳታፊ፣ ቦይኮት፣ መሥፈርቶች በተሻለ ሁኔታ የሚሟሉበት ሁኔታ...ወዘተ» የሚሉት ሐረጐች ከተፃፉባቸው መስመሮች ውጪ ምን ማለት እንደሆኑ ከሚያውቃቸው ሌላ ሊያውቃቸው አይችልም:: መጽሐፉ ለትውልድ የሚቆይ መልዕክት ይዞ መቆየት አለበት::

ዶ/ር ነገደ ጐበዜ ይበልጥ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለው ስለሚከራከሩበት ጉዳይ ስለ አገራችን ሕገ-መንግሥት አመጣጥና ምንነት በጥቅሉም ቢሆን ለሚፈለገው መልዕክታቸው በቂ ነው ብለው የገመቱትን መንደርደሪያ ጽፈውታል:: ይህንንም በ3 ዓበይት ክፍሎች ማለትም፣

I. ሕገ-መንግሥት ከንጉሡ እስከ ደርጉ
II. የምርጫ ሥርዓትና ሕገ-መንግሥታዊ ሂደት
III. የኢሕአዴግ ስታሊናዊና አደገኛ ሕገ-መንግሥት ብለው መድበው ስለ አገራችን ሕገ መንግሥት ይዘት ከአፄ ኃይለ ሥላሴ እስከ ኢሕአዴግ መንግሥት ያለፈበትን መንገድ እየገመገሙ ያስቃኙናል::

የደራሲውን ፍላጐት ገልጫለሁ:: የመጽሐፉን ይዘት ዓይነት ብጠየቅ ላጥ አድርጌ በፍጥነት የምሰጠው መልስ አለኝ ብዬ በርግጠኝነት መናገር አልችልም:: ልቦለድ (የፈጠራ ሥራ) ቢሆን ኖሮ ጭብጡ፣ ሤራው፣ የአጻጻፍ ዘዬው (Style)፣ አደረጃጀቱ (መቼቱ)፣ ቋንቋው፣ ገፀ ባሕርይ አቀራረጹ ...ወዘተ እያልኩ በሄድኩ:: የተለመደ ዓይነት የታሪክ መጽሐፍ ቢሆን፣ በመጽሐፉ የተሸፈነው ጊዜ (ዘመን)፣ ድርጊቶች በምን ያህል ጥልቀት ተስተናግደዋል? የታሪኩ የመረጃ ምንጮች የትኞቹ ናቸው? ትረካው አጠቃላይነት ወይስ ዝርዝርነት አለው? አፃፃፉ ሪፖርታዊ ወይስ ትርጉማዊ? የደራሲው አስተያየት ምንድነው? ያስተናገደው ርዕስ በለብ ለብ ዓይነት (superficial) ነው ወይስ አበጥሮ (Profound) ነው የጻፈው ... ወዘተ እያልኩ በዘረዘርኩ ነበር:: ይኸኛው ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ታሪካዊ መረጃ ሰጪ ድርሰት ስለሆነ በበኩሌ ተራኪና አስተማሪ መጽሐፍ ነው ብዬ ባካትተው ይመቸኛል::

ይህንን የምለው አንድ «ገላጭ አስተያየት» ሰጪ ማድረግ ከሚገባው ነገሮች አንዱ የደራሲው ዓላማ ምን ስሜት ፈጥሮበት እንደሆነ መግለጽ ስላለበት ነው::

ሕገ መንግሥት መኖሩ ብቻ አይበቃም በዶ/ር ነገደ ጐበዜ እንደተ ጠቀሰው:: ዴሞክራሲያዊ ይዘት ሊኖረው ግድ ይሆናል:: በአፄ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድ «ለሚወዱት ሕዝባቸው ከሰጡት» ሕገ-መንግሥት ጀምሮ ባለፉት 70 ዓመታት ስለ ዴሞክራሲና ስለ ሰብዓዊ መብቶች እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ድረስ ብዙ ትግል ተካሂዷል:: ኢትዮጵያ ግን እስከ ዛሬ ድረስ እውነተኛ ነፃነት ኖሯት አያውቅም:: የዚህ መገለጫውም መንስዔውን ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አለመኖሩና ባለመኖሩ ነው:: እንዲኖርም ስለ ሕገ-መንግሥት ይዘት የረባ ትግል ተደርጐ አያውቅም::

ያለፉት ተከታታይ ሕገ-መንግሥታት ወይ «በስጦታ» ወይ ደግሞ ለማስመሰልና ለድርጅት ሥልጣን ማጠናከሪያ ይሁን ተብለው ዲዛይን ተደርገው የወጡ ናቸው:: ደራሲው በመጽሓፋቸው የሚያስረዱት ይህንኑ ነጥብ ሲሆን ካሁን በኋላም ቢሆን ለዴሞክራሲ ሕገ መንግሥት ትግል ካልተደረገ ነፃ ኢትዮጵያ እየተባለች በምትጠራው አገራችን እውነተኛ ነፃነት ፈጽሞ ሊኖር አይችልም ነው ክርክራቸው:: የሕግ ሁሉ የበላይ የሆነው ዜጐች በአንድ አገር፣ በአንድ መንግሥት፣ በአንድ ግዛት ክልል አብረው ለመኖር ተስማምተው የሚፈርሙት «የውል ሰነድ» (ሕገ-መንግሥት) አወቃቀሩ ዴሞክራሲያዊነት ከሌለው ለገዢው ክፍል መጠቀሚያ የይለፍ ወረቀት ነው የሚሆነው:: በእንደ ዚህ ያለ ሕገ መንግሥት የሚከናወን ምርጫ የዜጐችን ነፃነትና ዴሞክራሲ መብት ሊያስከብር ይችላል ማለት ዘበት ነው:: ገዢው ፓርቲ የሚፈጽማቸውን የፖሊሲ ስህተቶችና አድሎአዊ አሠራሮች እየመዘዙ፣ እያወጡ ነቀፋና ሒስ መሰንዘር የተቃዋሚ ወገኖች ትኩረት ይሆንና ቁጭ ይላል:: በዋናው ጉዳይ ላይ ሳይሆን በጭፍጫፊው፣ በይዘቱ ሳይሆን በቅርጹ ላይ መረባረብ ይመጣል ማለት ነው::

ከዚህ ጋር በተያያዘ ዶ/ር ነገደ ሲገልጹ፣

«ዛሬ ትግላችን ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት በሚል ሳይሆን የመንግሥትን ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች በመዋጋት ላይ ያተከረ ሲሆን ከዚህ ጀርባ ያለው «አለመግባባት» በጣም ግልጽ ይመስለኛል:: በኅብረተሰባችን ፊት የተደቀኑት ችግሮች ከሕገ-መንግሥቱ ሳይሆን ኢሕአዴግ «የገዛ ሕገ-መንግሥቱን ካለማክበሩ» የሚመነጩ ናቸው ብለው የሚያስቡ ብዙ ወገኖቻችን አሉ:: ... በመሆኑም ትግላቸው እስከዘላለም ይህ ሕገ-መንግሥት እንዳለ ተቀ ይሮ በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት እንዲተካ ሳይሆን ወያኔ «ለራሱ ሕገ-መንግሥት ተገዥ እንዲሆን» (በሚል) መሟገት ሆኖ እናገኘዋለን::» በማለት አሁን ያለውን መሠረታዊ የግንዛቤ ችግር ያስረዳሉ:: የደራሲው ክርክር የሕገ-መንግሥቱ ይዘት ዴሞክራሲያዊ አለመሆን ነው:: በአንድ አንቀጽ የተሰጠው መብት በሌላ ቦታ በሌላ አንቀጽ ስለሚሻር ኢሕአዴግ እንደፈለገ ሊጠቀምበት የሚችል ላይ ላዩን ሲያዩት ለዜጐች መብት እውቅና የሰጠ መስሎ ለገዢው መደብ እንዲመች ሆኖ የተቀረጸ ነው የሚሉት...

በዶ/ር ነገደ አመለካከት ይህ መሠረታዊ የሕገ-መንግሥት ዴሞክራሲያዊነት ጥያቄ በአጠቃላይ በምሁራንም፣ በሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ ቸል ተብሏል::

«... የሕገ-መንግሥት ጥያቄ <የኤክስፐርቶች> ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ዴሞክራቶችን፣ አገር ወዳዶችንና ምሁራንን ሁሉ የሚመለከት

ጥያቄ ነው... በውጭም በውስጥም ያሉ የሀገራችን ዴሞክራቶች በየመስላቸው እየተደራጁ በፖለቲካውም በዲፕሎማሲውም መስክ <ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት> በሚለው ጥሪ ሥር እስከ ግንቦት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ለሚቀጥው ትግል...» መሆን እንዳለበት ነው የመጽሐፋቸውን ዓይነተኛ ግብ አድርገው የተነሱት:: ዶ/ር ነገደ እንደ መንደርደሪያ የመከራከሪያ ነጥብ ያደረጉት በደርጉም በኢሕአዴግም ሕገ-መንግሥቱ የተረቀቀው «ብሕዝባዊ ተሳትፎ ነው» የሚለውን «የማወናበጃ» ቃል ነው::

በደርግ ጊዜ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቁልቁል በወረደ መመሪያ ከሞላ ጐደል ቃል በቃል የተገለበጠው የሶቭየት ኅብረቱ ሕገ-መንግሥት ነበር:: በአዲሶቹ ገዢዎች «ብሕዝባዊ ተሳትፎ የተረቀቀ» እየተባለ የሚለፈፍለት ሕገ-መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በሌሉበት ሕዝቡ የሰጠው አስተያየት መካተቱን ማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነበረው ለማለት እንደማይቻል ለማስረዳት ይሞክራሉ::

የመጀመሪያው ሕገ-መንግሥት ዓላማ ንጉሡ የፊውዳሉን ሥርዓት በቁጥጥር ሥር በማድረግና ማዕከላዊ መንግሥቱን ለማጠናከር ሕዝቡ «ሳይጠይቅ» በንጉሡ መልካም ፈቃድ «የተሰጠ» ሰነድ ነበር:: ይህንን ዓላማ ግርማዊነታቸው በአገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ የመጀመሪያውን ፓርላማ ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ጠቅሰውታል::

«ኢትዮጵያ እንደ አንድ ቤተሰብ አንድነቷ የፀና የማትከፋፈል መሆን አለባት:: ከእንግዲህ ወዲያ አገሪቱ ለሁሉም የጋራ በሆነ በአንድ ሕገ-መንግሥትና በአንድ ንጉሠ ነገሥት የበላይነት ሥር መተዳደር ይኖርባታል»

ይህ አገላለጽ የሕገ-መንግሥቱን ዓላማ ይገልጻል:: ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው ዴሞክራሲያዊ ነበር ማለት አንችልም:: ሕገ መንግሥቱ በወጣበት ዘመንና ከዚያም በፊት ከነበረው የፖለቲካ ድባብ አንጻር ስናየው ግን አሰባሳቢ ከመሆኑ ሌላ በሕገ-መንግሥት መተዳደር መጀመር በራሱ ያልነበረ አዲስና ዘመናዊ አካሄድ እንደነበር እንገነዘባለን::

ንጉሡና ባለሟሎቻቸው አንድ ውሳኔ ከሰጡ በኋላ ለውጭው ዓለም ፍጆታም ለሀገር ውስጥ ፀጥታና ደህንነት ጥበቃ ሲባል «ሕዝቡ መክሮ ዘክሮ» የወሰነው ጉዳይ ነው ለማሰኘት (ለማስመሰል) የተደረገ መሆኑን ማንም አይስተውም:: (ባለንበት ዘመን «ድርጅታዊ አሠራር» የሚባለው አካሄድ ዓይነት መሆኑ አይደል?)

ምርጫን በተመለከተ የመጀመሪያውን ሕገ- መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ለማስመሰል «የሕግ መምሪያው» ምክር ቤት አባላት በሕዝብ የተመረጡ ናቸው ይላል:: የሚያስገርመው ግን እነዚህ በሕዝብ «ይመረጣሉ» የሚባሉት አባላት ሕዝቡ ፖለቲካ ገብቶት ራሱ መምረጥ እስኪችል ድረስ የመምረጥ መብት የተሰጠው ለመኳንንቱ፣ ቀሳውስቱና የጦር መኰንኖች ብቻ የነበረ መሆኑ ነው:: የዚህ ዓይነት ፓርላማ ቁርጠተኝነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊነትን የተላበሰ የፖለቲካ ኃይል ነበር ማለት ያስቸግራል:: የአፄ ኃይለ ሥላሴ 25ኛ የዘውድ በዓል (ኢዮቤልዩ) ሲከበር እንደገና «የተሻሻለ ሕገ- መንግሥት» ወጥቶ ነበር:: ለውጡን ደራሲው ሲያስቀምጡት፣

«እዚህ ጥናት ላይ ለሚመለከተን «የሕዝብ ተሳትፎ» ጉዳይ የተሻሻለው ሕገ- መንግሥት ያመጣው ትልቁ ለውጥ በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላላ የሕዝብ የመመረጥና የመምረጥ መብት ወይም ዩኒቨርሳል ሰፍሬጅ መፈቀዱ ነበር» በማለት አስፍረውታል:: ይህ «መሻሻል» ተደርጐበታል የተባለው ሕገ መንግሥት ግን ስለባላባቶቹ የኢኮኖሚ ኢፍትሐዊነት የጠቀሰው ነገር ስላልነበረ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ለውጥ አላስከተለም ነበር:: እንዲያውም ባለባቶችና ባለገንዘቦች በምርጫው መብት እየተጠቀሙ ገበሬውን በምንም በምንም እየደለሉ በመመረጥ ፓርላማ ውስጥ ገብተው ተጠናክረው ቁጭ ነው ያሉት:: ለዚህ መጠናከር እንደማስረጃ የጠቀሷቸው ሁለት ረቂቅ አዋጆች ሲጠቀሱ ይችላሉ::

«...የመጀመሪያው በሥራ አስፈጻሚው ክፍል ተረቅቆ ከ1954 ጀምሮ በየጊዜው ለፓርላማ እየቀረበ ሲጠና፣ ሲሻሻልና ጨርሶ ሲረሳ የ1966 አብዮት የደረሰበት የጢሰኛና የባለርስት ግንኙነት ማሻሻያ ሕግ» ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1958 የገንዘብ ሚኒስትር በነበሩት በአቶ ይልማ ዴሬሣ ቀርቦ የአካባቢ ፊውዳሎችን ጥቅም በመንካቱ ሥቃዩን ያየው የታክስ ማሻሻያ ሕግ ነበር::»

በማለት ሕገ- መንግሥቱ ዴሞክራሲያዊ እንዳልነበር የሚያስረዱትን ሁለት ረቂቅ ሕጐች በመጽሐፋቸው ውስጥ ጠቅሰዋል::

የንጉሡ አገዛዝ ከተወገደ በኋላስ የሕገ- መንግሥት ዴሞክራሲያዊነት ጥያቄ እንዴት ነበር የተመለሰው:: ባጭሩ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር:: እንዲያውም የትግሉ አቅጣጫ በአንድ ፓርቲ እንተዳደር ወይስ በመድብለ ፓርቲ? በሚሉት ነጥቦች ላይ ነበር ያተኮረው:: በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኰንን ተረቆ የቀረበው ሕገ- መንግሥት የዘውድ አገዛዝ እንደ እንግሊዞች እንዲቀጥል የሚደግፍ ነበር:: ቀጥሎ ደግሞ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት» የሚል ሠነድ ወጣ:: በታህሣሥ 11/67 ምሽት ላይ ደግሞ «ኅብረተሰብዓዊት ኢትዮጵያ» የሚለው የአንድን ፓርቲ ብቻ አገዛዝ የሚያፀድቀው አዋጅ ተነገረ:: ሕዝቡን በቀጥታ የሥልጣን ተሳታፊ የሚያደርግ ሠነድ አልነበረም::

እዚህ ላይ ዶክተር በዝርዝር ያላስቀመጡት ነገር ቢሆን እነዚህም ሰነዶች ቢኖር የውጭ ግልባጮች (ባዕድ ሐሳቦች) መሆናቸውን ነው:: ሶሻሊዝምና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት የሚባሉ መርሆች እንኳን ለሰፊው ሕዝብ ከጥቂቶች በስተቀር ለብዙኃኑ ምሁራን አዲስ ሐሳቦች ነበሩ:: ከዚህ አንፃር ሲታይ እንዲያውም በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው የቀረበው ረቂቅ ዘውዱን ለምልክትነት ጠብቆ «ሪፐብሊክ»ን በሕዝብ ምርጫ ማቋቋም የሚለው እምብዛም ሩቅ አልነበረም ማለት ይቻላል:: ይልቁንም ለዘመናት ተንሠራፍቶ የቆየን ሥርዓት መለወጥ የሚቻለው ስትራተጂክ በሆነ መንገድ ስለሆነ «አዝጋሚና የጥገና ለውጥ» የሚል አጉል ስም ቢያሰጥም ምናልባት ከጊዜው ጋር እንዲራመድ ቢደረግ ኖሮ ውጤቱ በኋላ ከደረሰው ሁኔታ የተሻለ ሊሆን ይችል እንደ ነበር ብዙዎች በፀፀት የሚያነሱት ነው::

ከዚህ ጋር በተያያዘ ንጉሡ ከሥልጣን እንዲወርዱ ከመደረጋቸው በፊት ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፣ «በኢትዮጵያ የዘውድ አገዛዝ ከጊዜው ጋር መራመድ አለበት:: ... ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ነገሥታት አቋም የሚወሰነው በሕዝቡ ጥያቄና ፍላጐት ይሆናል:: ከእንግዲህ የመንግሥት ተቋሞቻችን ሁሉ መገንባት ያለባቸው ሕዝቡ እየተስማማባቸው መሆን ይኖርበታል:: ሌላው ቀርቶ ለነገሥታቱ የሚታወቅላቸው ሥልጣን ራሱም ቢሆን በሕዝባችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት::» የሚል የወቅቱን የዴሞክራሲ ጥያቄ ያስተናገደ መልእክት ነበር ያስተላለፉት:: «የሕዝብ ተሳትፎ» በየሥርዓቱ መጠቀሱ አልቀረም:: ሕዝቡ በተግባር የተሳተፈበትና የራሱ ባለቤት ሆኖ የሥልጣን ተጋሪ የሆነበት ዕድል ግን እስከ ዛሬ አላገኘም ነው በዶክተር ነገደ ጐበዜ ትንተና:: ደርግም ሥልጣን እንደያዘ አካባቢ «ተሻሽሎ» የወጣው ሕገ- መንግሥት በሥራ ላይ ይውላል ሲል ይፋዊ መግለጫ ሰጠ::

በመካከሉ የአብዮቱ ማዕበል አገሪቱን ከዳር እስከ ዳር በማጥለቅለቁ የሰከነ እርምጃ መውሰድና ሕገ- መንግሥትን በተግባር ለመተርጐም «ፋታ» ቢጠየቅም ፋታ አልተገኘም:: እያንዳንዱ ዕለት አዳዲስ አዋጆች የሚሰሙበት ወይም የሚናፈቁበት ጊዜ ነበር:: ስለሆነም ውይይት ሳይደረግበት እንዲሁ በስሜት ብቻ «የዘውድ» ስም ለምን ተነስቶ በሚል ብቻ ተቃውሞው ተጧጧፈ:: ነገሮች መልካቸውን እየለወጡ ሄደው ደርግ ተቋቋመ:: ከዚያ በኋላ በሂደት ጥያቄው ዴሞክራሲያዊ ሕገ- መንግሥት መሆኑ ቀርቶ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት፣ አንድ ፓርቲ፣ መድብለ ፓርቲ በእርሶ አደሩና በወዝ አደሩ ትብብር ወዘተ...» የሚል ሆነና የትኩረቱ አቅጣጫ ተቀየረ:: ለውጥ፣ ለውጥ ሲባል ቆይቶ ከምጣዱ ወደ እሳቱ፣ ከድጡ ወደ ማጡ ተገባና አረፈ:: በማከያው ላይ ወታደራዊው መንግሥት የሆነ ሠነድ አዘጋጅና ሌሎቹን ተራማጆች በተለያዩ መንገዶች አባርሮ አረንጓዴ ካኪውንና መለዮውን አውልቆ ሰማያዊ ካኪውን ግጥም አድርጐ ለብሶ ፓርቲ ነኝ ብሎ ቁጭ አለ:: ስለዚህ ጉዳይ ዶ/ር ነገደ ሲጽፉ፣

«...9 ሚሊዮን ሕዝብ እያስራበ፣ 2 ሚሊዮን ሕዝብ ለስደት ዳርጐ፣ የኢትዮጵያን ወዝ አደሮች መብት እንዳልነበር አድርጐ ረግጦ የሀገራችንን ክብሯንም ነፃነቷንም ለባዕዳን የሸጠ የቅምጦች መንግሥት ራሱን «የሠርቶ አደሮች ፓርቲ» ብሎ ስለሰየመ ብቻ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለው ምንም ተዓምር አልነበረም::» ይላሉ::

ደራሲው በክፍል 3 የገለጹት የወታደራዊው መንግሥት ሕገ- መንግሥት ከሶቭየት ኅብረት ሕገ- መንግሥት የተገለበጠ መሆኑን የሚያጋልጥ ጽሑፍ ነው:: ስለ ሕገ- መንግሥት ፅንሰ ሐሳብ ያቀረቡት ማብራሪያ እንድ ሕገ- መንግሥት ዴሞክራሲያዊነት ሊኖረው ይገባል ብለው ከመጀመሪያው የተነሱበትን ዓላማ ለማብራራት በጣም ጠቃሚ መረጃ ይመስለኛል:: በዚህኛው ክፍል ከ18ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በአሜሪካና በፈረንሣይ የከበርቴ አብዮቶችን ተከትሎ የተፃፈ ሕገ- መንግሥት ሥራ ላይ መዋል መጀመሩን ያብራሩና የሶቭየት ኅብረትንም ሕገ- መንግሥት አመጣጥ እያይዘው ሰፋ ያለ ዘገባ ይሰጣሉ:: በዚህ ትንተናቸው ውስጥ ሕገ- መንግሥት በማን እንደሚረቀቅ፣ እንዴት አድርጎ ለሕዝብ ውይይት እንደሚቀርብና መሻሻልም ካለበት እንዴት እንደሚሻሻል ያስረዳሉ:: ከዚያም የሕዝቡ መስመራዊና ዓምዳዊ የሥልጣን ውክልና እንዴት እንደሚሠራና «የመንግሥት የሕግ ማውጣት የሥራ (የሕግ) ማስፈፀምና የቁጥጥር ተግባራት» እንዴት ተጣቃሎ እንደሚይዝ ያስቀምጣሉ:: የተለያዩ አገሮችን ማለትም የቡልጋሪያን፣ የሀንጋሪን፣ የምሥራቅ ጀርመንን የፓርላማ ሥልጣን ውክልና ከአገራችን ሁኔታ ጋር እያነፃፀሩ ያቀርባሉ::

መጽሐፉ ሰፋ ባለ መንገድ የሚዘግበው ደራሲው «ስታሲናዊ» ስለሚሉት የኢሕአዴግ ሕገ- መንግሥት ነው:: በርካት ያሉ (18 በቁጥር) የምዕራብ ሊበራል ዳሞክራሲ መንግሥታት «በአነዳደፍ ሂደቱም ሆነ በይዘቱ» ኢዲሞክራቲክ የሆነውን የወያኔን ሕገ- መንግሥት

ዴሞክራሲያዊ ነው ከማለት አልፈው «በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ዘር ተዘርቷል» እስከማለት መድረሳቸውን «አስደናቂ መግለጫ» ብለውታል። ምክንያታቸውንም ሲያቀርቡ ማንኛውም ሕገ-መንግሥት መያዝ ያለበትን እንደ «ሥልጣን ክፍፍል፣ እንደ ዳኝነት ነፃነት፣ እንደ ሕገ-መንግሥታዊ ቁጥጥር፣ እንደ መድበለ ፓርቲ ሥርዓት» የመሳሰሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች በየትኛው አንቀጽ እንደተረጋገጡ ያሳዩን ሲሉ ጠይቀዋል። እነዚህ መንግሥታት ትናንት ከተጠየፉት ከደርግ ሕገ- መንግሥት በምን እንደሚለይና ምኑ «ዴሞክራሲያዊ» እንደሚያሰኘ ቢያስረዱን መልካም ነበር ሲሉ የምራባውያኑን መንግሥታት ድጋፍ አጣጥለውታል። ሕገ-መንግሥቱን ስታሊናዊ በማለት ሲያብራሩ፣ «ይህ ሕገ- መንግሥት እንደ ትላንቱ የደርግ ሕገ- መንግሥት ስታሊናዊ ነው የምንለው በሂደቱም ሆነ በይዘቱ የማንኛውንም ዴሞክራሲያዊ ሕገ- መንግሥት የማርቀቅ ሂደትና ይዘት መስፈርቶች ባለማሟላቱ ብቻ አይደለም።» ይሉና አያይዘውም ስለ አደገኛነቱ ያላቸውን ሥጋት ሲገልጹ፣

«ሕገ- መንግሥቱ ለዴሞክራሲና ለሀገራችን ሰላም አደገኛ ነው የምንለው የፖለቲካ አወቃቀሩ፣ የኢኮኖሚ ንጣፉና የብሔር ብሔረሰብ ችግር በመሳሰሉት ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ የአንድን አናሳ ኃይል ፀረ- ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም «የሀገር የበላይ ሕግ» አድርጉ በመጫኑ ብቻ ሳይሆን በሩን ለፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በርግዶ መክፈቱ አንሶ በዚያው ልክ ለሰላማዊ የለውጥ ሂደት ደግሞ ጥርቅም አድርጉ በመዝጋቱም ነው» *በማለት የሕገ- መንግሥቱን ኢ- ዴሞክራሲያዊነት ለማስረዳት ይሞክራሉ።*

*ይህንኑ መንደርደሪያ ሐሳብ አስከትለው በስታሊናዊ ሕገ- መንግሥት 1) ሕዝብ ለገገርዎች ወይስ ገገርዎች ለሕዝብ የሚሰጡት ሠነድ? 2) የሥልጣን ክፍፍል ወይስ የሥልጣን አንድ ወጥነት 3) የዳኝነት ነፃነት ጥያቄ 4) የሕግ የበላይነትና የሕገ- መንግሥት ቁጥጥር ጥያቄ በሚሉ ንኡሳን ርዕሶች ከፋፍለው ሰፋ ያለ ማብራሪያቸውን አቅርበዋል። ከዚያም በመቀጠል ስለ*

*- ሕገ- መንግሥት ሕግ ወይስ ፕሮግራም?*

*- «ዴሞክራሲያዊ ፌዴሬሽን» ወይስ ፈላጭ ቆራጭ አሀዳዊነት? በሚሉ ርዕሶች ላይ ትንተና በመስጠት ለውይይት ጋባዥ የሆኑ ጥያቄዎችን አንስተዋል።*

*በዶክተር ነገደ ጐበዜ አመለካከት አንዳንድ ሰዎች በአንቀጽ 39 ምክንያት የኢሕአዴግ ሕገ- መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሊመስላቸው ይችላል ይሉና፣*

*«የሶቭየት ሕገ- መንግሥት በአንድ አገር ውስጥ ሁለት ፓርቲዎች ሳይፈቅድ በአንድ ፓርቲ ሥር ከሁለት በላይ አገሮች የሚተዳደሩብትን አወቃቀር የደነገገ «እንግዳ» ሕገ- መንግሥት ነበር» ይሉና ወደ አገራችን ሕገ- መንግሥት መለስ ብለው፣*

*«የኢሕአዴግም ሕገ- መንግሥት ... የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እስከመገንጠል አውቃለሁ ማለቱ ፈላጭ ቆራጭ አሀዳዊነቱን ሊሸፍንለት አይችልም። የግለሰቦችን ሰብዓዊና መሠረታዊ መብቶች ዋስትና ባለው ሁኔታ ሳያረጋግጥ የሕዝቦችን መብት አውቃለሁ ብሎ ስለ ለፈፈና አልፎ ተርፎም ከፈለጋችሁ የራሳችሁን ሉዓላዊ መንግሥት የማቋቋም መብት አላችሁ ስላለ ብቻ ዴሞክራሲያዊ ሰነድ ነው ተብሎ የሚጠራበት ምንም መለኪያ የለም» ሲሉ ይደመድማሉ።*

## *ማጠቃለያ*

*ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት «ገላጭ አስተያየት» የመጽሐፍ ማጠቃለያ አይደለም። ስላልሆነም ከወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ጥያቄ ጋር አግባብነት ካላቸው ገጽታዎች መካከል በጥቂቶቹ ላይ የመጽሐፉን መስተንግዶ ለማንሳት ሞክሬያለሁ። ዓላማዬ ቅስቀሳ ስላልሆነ ዶ/ር ነገደ መጪውን ምርጫ አስመልክቶ «እንግዲህ ምን እናድርግ?» ሲሉ መልሱ ግልጽ የሆነውን ጥያቄ እዚህ ማንሳት ያለብኝ አልመሰለኝም።*

*የግምገማ ወግ ነውና አስተያየት መስጠት ይኖርብኛል። በኔ አስተያየት ሕገ-ንግሥት ሲነደፍ በአብዛኛው ሕዝብ ተሳትፎ ዴሞክራሲያዊ ይዘት እንዲኖረው ያስፈልጋል የሚለው ሐሳብ ምርጫም አይመስለኝም። ሀገራዊ ኃላፊነትና የዜጐች ግዴታም ጭምር ነው። የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። እዚህ ላይ ለዶ/ር ነገደ የማቀርበው ጥያቄ ይኖረኛል። በወረቀት ላይ የምንፈልገው ነገር ሁሉ ቢሰፍር ካልተሠራበት ምን ዋጋ አለው? አንድ ሕገ-መንግሥት የተጻፈበት ዓላማና አጀንዳ ተረስቶ ነው ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመቀየር ሕዝባዊና ሰላማዊ ትግል መደረግ አለበት የምንለው? ወይስ ለመሄድ መጀመሪያ የት እንዳሉ ማወቅ መቅደም ያለበት ይመስለኛል። በምን ላይ ቆመን ነው ዴሞክራሲያዊነትን የተላበሰ ሕገ-መንግሥት የምንቀርፀው? አስተያየቴን ከማጠናቀቄ በፊት ደንብ ነውና ከመጽሐፉ ጋር አግባብነት የላቸውን የዳራ መረጃዎች ብቻ በመጥቀስ ደራሲውን ዶ/ር ነገደ ጐበዜን ከአንባቢ ጋር ማስተዋወቅ ተገቢ ይመስለኛል።*

*ዶ/ር ነገደ የተወለዱት በ1935 ዓ.ም ደሴ ነው። በወ/ሮ ስህን ት/ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው አዲስ አበባ መጡና ጄኔራል ዊንጌት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ገቡ። ቀጥለው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (UCAA) የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በ1964 በኢኮኖሚክስ አገኙ። በዚያው ዓመት የነፃ ትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ፈረንሣይ ሄዱ።*

*ደቡብ ፈረንሣይ በሚገኘው ማርሴይ ዩኒቨርሲቲ ገብተው እ.ኤ.አ ከ1964 እስከ 1974 የሕግ ትምህርታቸውን ሀ ብለው ጀምረው እስከ ዶክትሬት አጥንተው ተመረቁ። የመመረቂያ ጽሑፋቸው በሕገ-መንግሥት ሕጐች ዘርፍ «ፓርላማዎችና በአፍሪካ ባሕላዊ ማኅበረሰብ በሚል ንኡስ ዘርፍ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛትና የታንዛኒያ ሪፐብሊክ መንግሥታት ንፅፅር» በሚል ርዕስ ላይ ነበር የጻፉት።*

*ዶ/ር ነገደ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር። ለበርካታ ዓመታት የ«ታጠቅ፣ ትግላችን፣ የትግላችን ዜና» የሚባሉት እትሞች በኤዲቶሪያል ቦርድ አባልነትና በአዘጋጅነት አገልግለዋል። እ.ኤ.አ በ1968 ነሐሴ ወር ጀርመን አገር ሀምበርግ ላይ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ሲቋቋም ከመሥራች አባሎች አንዱ ነበሩ።*

*በአብዮቱ ማግስት ወደ አገራቸው ተመልሰው የድርጅቱ የዓለማቀፍ አሳታሚዎች ዳይሬክተር፣ የሕዝብ ድርጅት የፍልስፍና ማስፋፊያ ኃላፊ፣ የየካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት ሱፐርቫይዘር በመሆን ከእነ ኃይሌ ፊዳ ጋር ሠርተዋል። የግዮኑ የሰላም ኮንፈረንሱ ሰብሳቢም ነበሩ። ዶ/ር ነገደ ጐበዜ ባለትዳርና የ2 ሴቶች ልጆች አባት ሲሆኑ ባሁኑ ጊዜ አውሮፓ ውስጥ በስደት ይኖራሉ።*

# ለአገራቸውና ...

ከገጽ 24 የዞረ

*በአየር ኃይል ውስጥ ስልጥነው፣ አስፈላጊውን የማዕረግ ዕድገትና የሥልጣን ደረጃ ጠብቀው፣ የአካበቱትን ዕውቀትና የሥራ ልምድ በአግባቡ በመጠቀም፣ ፈታኝና አደናጋሪ ሁኔታ በበዛበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይልን በፀና አቋማቸውና አይበገሬ ጀግንነታቸው መርተው በማሳደግ አገራዊ ግዴታውን በተሟላ ሁኔታ እንዲወጣ አድርገዋል።*

*ከተማሪነት አንስቶ እስከ አየር ኃይል አዛዥነት በቆዩባቸው ዓመታት፣ ሁለገብ ችሎታቸውን ሁሉ አሟጠው በመጠቀም፣ ከሁሉም የሠራዊቱ አባላት ጋር ተቀላቅለው፣ ተስማምተውና ተከባብረው በእግር ኳስ፣ በመረብ ኳስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በግራውንድ ቴኒስና በሌሎችም የስፖርት ዓይነቶች ለረዥም ዓመታት በመጫወት ኃይሉን የተደጋጋሚ ድሎች ባለቤት እንዲሆን አድርገዋል።*

*በሰላሳ አራት ዓመት የአየር ኃይል አገልግሎት ዘመናቸው በበራሪነት፣ በተዋጊነት፣ በበራሪ አስተማሪነት፣ ከታች ጀምሮ በየደረጃው ያለውን የአዛዥነት ቦታ በመከተል የአየር ኃይል አዛዥ በመሆን በርካታ ፍሬያማ፣ አኩሪና አስመኪ ግዳጆችን በልበ ሙሉነት፣ በጠራና በፀና አቋም ተወጥተዋል።*

*በዓለም አቀፍ ተልዕኮም ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ወክለው በኮንጐ፣ እንዲሁም በጐረቤት ሱማሊያ የጐርፍ ማጥለቅለቅ አደጋ በደረሰበት ወቅት አውሮፕላን በማብረር የአልባሳትና የመድኃኒት ዕርዳታ በማድረስ በጉ ግልጋሎት ሰጥተዋል።*

*የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሁለገብ ዕድገት፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ አሠራር ሲወሳ ደግሞ እንደ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ወንዱ የመሳሰሉት ልበ ሙሉ፣ አርቆ አሳቢ፣ ታታሪ፣ ቆራጥና ምሁር የሠራዊቱ ፍሬዎች ከኃይሉ ጋር ተያይዘው ዘወትር ይዘከራሉ። የአገርንና የሕዝብን ጥቅምና ክብር ከመሪ ድክመት ለይቶ የማየት ችሎታና ብቃት የነበራቸው ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ወንዱ፣ የደርግን የለውጥ አካሄድና የአመራር ስልት ከመጀመሪያው አንስቶ አጥብቀው ይጠሉና ይነቅፉ የነበሩ ቢሆንም፣ በ1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር ኃይል የሁለተኛው አየር ምድብ አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በውስጥ አርበኞች አቀናባሪነት የተቀናጀውን የተገንጣዮች የአሥመራና የሌሎች ከተሞች ከበባ ጀግንነት በተሞላበት ከፍተኛ የአዛዥነትና የማስተባበር ብቃት የተከላካይነትና የአጥቂነት ተጋድሎ በመፈጸም በማስፈጸምና ከበባው እንዲሰበር አድርገዋል። እንዲሁም ለብዙ ዓመታት ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግ የቆየው የጐረቤት ሱማሌ ጦር በ1969 ዓ.ም የኢትዮጵን ወሰን ጥሶ በአየር፣ በታንክና በመድፍ እየታገዘ እግረኛ ሠራዊቱ፣ የወገንን ደጀን ሰብሮ የዕዝ ቁንጮዎችን በመውረር በየደረሰበት ቦታ ሁሉ አውሮፕላኖችንና ሌሎች ንብረቶችን እያቃጠለ በገፋበት ወቅት፣ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ በከፍተኛ ጀግንነት፣ ድፍረት፣ ቆራጥነትና ብልሃት የአካባቢውን እግረኛ ሠራዊት ሳይቀር ከአየር ኃይሉ ጋር አስተባብረው፣ መርተውና አዝዘው ሁሉም ተዋጊና ድጋፍ ሰጭ አውሮፕላኖች በጠላት እጅ*

ወደ ገጽ 35 ዞሯል